
«የጌታንም ድምፅ፦ ማንን
እልካለሁ? ማንስ
ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ።
እኔም፦ እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ
አልሁ።»
(ኢሳይያስ 6:8)

የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ነቢይ በሆነው በአብርሃምና በአዲስ ኪዳን የመጀመሪያውን ነቢይ በመጥምቁ ዮሐንስ መካከል ወደ 1,900 የሚደርሱ ዓመታት አሉ።

የመጀመሪያው ነቢይ በ “ዘሩ” በኩል ስለሚመጣው ኪዳን አውጆ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ቃል የተገባውን ኪዳን የሚፈጽመውን “ዘር” ወይም የኢየሱስን መገለጥ አውጆ ነበር።



በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘትና የመሲሑንም መምጣት ለማመልከት ሌሎች ብዙ ነቢያት ተጠርተው ነበር። አንዳንዶች መሲሑ የሚመጣበትን ጊዜ ሳይቀር በትንቢት ተናግረው ነበር።

እነዚህ ነቢያት የተመረጡት እንዴት ነበር? ለመጣላቸው የነቢይነት ጥሪስ ምላሽ የሰጡት እንዴት ነበር?




- አብርሃም: የኪዳኑ ነቢይ
- ኤልያስ: የመታደስ ነቢይ
- ኢሳይያስ: መሲሐዊው ነቢይ
- ዳንኤል: የወደፊት ዘመናት ነቢይ
- መጥምቁ ዮሐንስ : ከፊት የሚሄደው ነቢይ

# አብርሃም: የኪዳኑ ነቢይ

"እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።" (ዘፍጥረት 12:1)

አብርሃም "ነቢይ" ተብሎ የተጠራው የመጀመሪያው ሰው ነው (ዘፍ 20:7)። በዙሪያው ከከበበው ጣዖት አምልኮና ክፋት ወጥቶ ወደ ማይታወቅ ሥፍራ እንዲሄድ እግዚአብሔር በቀጥታ የጠራው ሰው ነው (ዘፍ 12:1)።



ከዚህም ተስፋ ጋር አብረው ብዙ ተስፋዎች መጥተውለት ነበር። እግዚአብሔር እንደሚባርከው፣ እንደሚያከበረው እና በእርሱ በኩል "የምድር ሕዝቦች በሙሉ" እንደሚባረኩ ቃል ገብቶለት ነበር (ዘፍ 12:2-3)።





ለጥሪው ምላሽ የሰጠው እንዴት ነው? "አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ።" (ዕብ 11:8)

አብርሃም እንደ ነቢይ የተጠራው ስለ አንድ መፃዒ ጥፋት ለማስጠንቀቅ ሳይሆን እውነተኛውን አምላክ ለማሳወቅና በመሲሑ በኩል የሚመጣን የመዳን ተስፋ ለመግለጥ ነበር።

# አብርሃም: የኪዳኑ ነቢይ

"እግዚአብሔርም አብራምን አለው፡- ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።" (ዘፍጥረት 12:1)

አብርሃም በከነዓን ቆይታው እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ተገልጦለት ነበር፣ ብዙ መልዕክቶችንም ሰጥቶት ነበር:



በሴኬም ዘሮችህ የከነዓንን ምድር ይወርሳሉ ተብሎ ተነግሮለት ነበር (ዘፍ 12:6-7)



በቤቴል እግዚአብሔር ዘሮቹን እንደ "ምድር አሸዋ" እንደሚያበዛ ነግሮት ኪዳኑን አደሰለት (ዘፍ 13:14-18)



በመምሬ ዘሮቹ እንደ ከዋክብት እንደሚበዙ ተነግሮለት ነበር። "አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።" (ዘፍ 15:1-6)



እግዚአብሔር በዚያኑ ሰዓት ከአብራም ጋር ቃል ኪዳን ገባ፣ በተሰነጠቁት እንስሳት መካከልም በእሳት አለፈ (ዘፍ 15:7-21)



እግዚአብሔር የአብራምንና የሦራን ስም ቀይሮ ወራሹ የሣራ ልጅ እንደሚሆን አረጋገጠለት (ዘፍ 17:1-8፣ 15-16)



እግዚአብሔር ከሁለት መላዕክት ጋር ለአብርሃም በአካል ተገልጦ የይስሃቅን መወለድ ነገረው (ዘፍ 18:1-2, 10)



እግዚአብሔር አብርሃም ልጁን እንዲሰዋ ጠየቀው። ከዚያ ግን በምትኩ የሚሰዋ በግን አዘጋጅቶ ታላቁን የመዳንን ሥራ ለእርሱ ገለጠለት (ዘፍ 22:1-3፣ 9-13)።

# ኤልያስ፡ የመታደስ ነቢይ

"ኤልያስም ወደ ሕዝቡ ሁሉ ቀርቦ፡- እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በኣል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ። ሕዝቡም አንዲት ቃል አልመለሱለትም።" (1 ነገሥት 18:21)



አካብና ኤልዛቤል የእስራኤልን ሕዝብ ወደ አደገኛ ክህደት ውስጥ ከትተው ነበር። ጥቂቶች ብቻ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ቀሪው አብዛኛው ሕዝብ ግን ለበአልና ለሌሎች አማልክት ይሰግዱ ነበር። እግዚአብሔር በዚያ ዘመን ከተመረጡት ሕዝቡ ጋር ግንኙነቱን ያድስ ዘንድ ነቢዩ ኤልያስን ጠራው (1 ነገ 17:1)።



ከብዙ የድርቅ ዓመታት በኋላ ኤልያስ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ሊያበረታታቸው እስራኤልን ሁሉ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጠርቶ ነበር (1 ነገ 18:21)። እውነተኛውን አምላክ ለመለየት ተዓምር ማየት ነበረባቸው (1 ነገ 18:30-39)።



ጣዖትን ማምለክ ትታችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ የሚለው የኤልያስ መልዕክት ከዳግም ምጽአቱ በፊት እንደገና በኃይል ይሰበካል። ዋና አላማውም የቤተሰብ መሰውያን ማደስ ነው (ሚል 4:5-6)።



በቤተሰብ በኩል የቤተክርስቲያን፣ የሕብረተሰብና የአሕዛብም አምልኮ ይታደሳል። ይህን ስራ የሚፈጽመው ማንነው? ለሕዝቡ የሚያስፈልገው ኤልያስ እኔና እናንተ ነን።

# ኢሳይያስ: መሲሐዊው ነቢይ

"እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።" (ኢሳይያስ 53:6)





ኢሳይያስ የተጠራው ሕዝቡ ኃጥያታቸውን አውቀው የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲቀበሉ እንዲመራቸው ነበር (ኢሳ 1:18)።

ንጉሥ ዖዝያን በሞተ ጊዜ ኢሳይያስ በዘመኑ ሁሉ የማይረሳውን አንድ አስደናቂ ራዕይ ተመልክቶ ነበር። እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ ውስጥ ሆኖ ሲመለክና የመድረኩ መሠረት ሲናወጥ በተመለከተ ጊዜ ነቢዩ የረከሰ መሆኑን በማስተዋሉ ልቡ ተንቀጠቀጠች (ኢሳ 6:1-5)።

ኃጥያቱም በፍም ይቅር ተባለለት። ከዚያም "እነሆኝ፣ እኔን ላከኝ" በማለት በድፍረት የእግዚአብሔርን መልዕክት ለማወጅ ተነሳ (ኢሳ 6:6-8)።

በረጅም የአገልግሎት ዘመኑ ንስሃን በመስበክ ብቻ ሳይሆን በተለየ መንገድ የመሲሑን የኢየሱስን ሕይወትና ሥራ የመተንበይ እድል አግኝቶ ነበር።





ከዚህም የተነሳ የኢሳይያስ መጽሐፍ "ቅድመ ወንጌል" በመባል ይታወቃል። ወንጌል ሳይገለጥ በፊት ወንጌልን በትንቢት ተናግሮ ነበር።



# ኢሳይያስ: መሲሐዊው ነቢይ



“እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።” (ኢሳይያስ 53:6)

ኢሳይያስ ምዕራፍ 53 የኢየሱስን የቤዛነት ሥራ በዝርዝር ያስረዳል:



መንፈሳዊ እንጂ አካላዊ ውበት አልነበረውም (ቁ. 2)



የተናቀ፣ የተጠላና የሕማም ሰው ነበረ (ቁ. 3)



ብዙዎችን ቢፈውስም ግን አልተቀበሉትም (ቁ. 4)



በመስቀል ላይ ሞቱ ለእኛ መዳንን አስገኝቷል (ቁ. 5)



እግዚአብሔር ኃጥያታችንን በሙሉ እርሱ ላይ ጫነው (ቁ. 6)



በከሳሾቹ ፊት እራሱን አልተከላከለም (ቁ. 7)



ክስ አቅርበውበት የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል (ቁ. 8)



መቃብሩ ከባለጠጎች ጋር ነበር (ቁ. 9)



ምንም በደል አልተገኘበትም (ቁ. 9)



ሥርየትን ካስገኘልን በኋላ ከሞት ተነሳ (ቁ. 10)



አንድ ቀን ከተቤዣቸው ጋራ በአካል ይኖራል (ቁ. 11)



ለኃጥያተኞችም ማለደ (ቁ. 12)

# ዳንኤል፡ የወደፊት ዘመናት ነቢይ

"ነገር ግን ምሥጢር የሚገልጥ አምላክ በሰማይ ውስጥ አለ፥ እርሱም በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ለንጉሡ ለናቡከደነፆር አስታውቆታል።" (ዳንኤል 2:28)



ገና ከጅምሩ ዳንኤል በታማኝነቱ ይታወቅ ነበር። በመብሉ ታማኝ ነበር (ዳን 1:8)፣ እግዚአብሔርን በማክበር ታማኝ ነበር (ዳን 2:27-30)፣ ለንጉሡም ታማኝ ነበር (ዳን 4:19)፣ ለንጉሥ ብልጣሶር በታማኝነት ኃጥያቱን ነግሮት ነበር (ዳን 5:22-23)፣እና በጸሎት ሕይወቱም ታማኝ ነበር (ዳን 6:10)።






በኑሮው ከሚያስተላልፈው መልካም መልዕክት በተጨማሪ የዓለም ታላላቅ መንግሥታት የሆኑትን የባቢሎንን፣ የፋርስን፣ የግሪክን፣ የሮምንና የአውሮፓን አነሳስና ውድቀት ተመልክቶ ነበር (ዳን 2፡ 7-12)።

ዳንኤል ከመንግሥታቱ ትንቢት ጋር ተያይዞ የፍርድን (ዳን 7:9-10) እና የኢየሱስን የመጀመሪያ መምጣት ትክክለኛ ጊዜ ተመልክቶ ነበር (ዳን 9:24-27)።







የዳንኤል ትንቢት ገና ሊፈጸም ያለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ምጽዓት ለማወጅ ይረዳናል (ዳን 2:44; 7:27)።

# መጥምቁ ዮሐንስ፡ ከፊት የሚሄደው ነቢይ

"እርሱም፡- ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ፡- የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።"
(ዮሐንስ 1:23)



እንደ ሳሙኤል፣ እንደ ኤርምያስ ወይም እንደ ሌሎች ነቢያት ዮሐንስም የተለየው ገና ከማሕፀን ነበር። ከመሲሑ ፊት በመውጣት የኤልያስን ሥራ እንዲሰራ ነበር የተጠራው (ሉቃ 1:13-17)።



የማይመች ኑሮ ቢኖርም ኃጥያትን በግልጽ በመቃወም በአስቸኳይ ወደ ንስሃ በመጥራቱ ብዙዎችን ወደ ጥምቀት መርቶ ነበር (ማር 1:4-6)። በዮሐንስ አገልግሎት ምክንያት በእስራኤል ውስጥ የመጣውን ታላቅ ለውጥ ሰይጣን እንኳን ሊይዘው ስላልቻለ የነቢዩን ሞት አስከትሎ ነበር (ሉቃ 9:9)።



ዮሐንስ የተወጣውን የኤልያስን ሥራ አሁን የምንሰራው እኛ ነን። የንስሃን ወንጌልና የኢየሱስን ሞትና ትንሳኤ በማመን የሚገኘውን መዳን ለሁሉም በመስበክ ለኢየሱስ ምጽዓት እንድንዘጋጅ ተጠርተናል።

መንገዱ አልጋ በአልጋ አይሆንም። መታመንን፣ መሰጠትን እና ቆራጥነትን ይጠይቃል። አደጋን ማስቀረት ባይቻልም የዘላለም ሕይወት ግን ለእኛም ሆነ መልዕክቱን ለሚቀበሉ ሁሉ የተረጋገጠ ነው።

“የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድ በገለጡት በነቢያት በኩል የተሰጡት የምክርና የተግሳጽ መልዕክቶች በወይኑ እርሻ ጠባቂዎች ለምትመሰለው በምድር ላይ ላለችው ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ልዩ ዋጋ አላቸው። እግዚአብሔር ለጠፋው የሰው ዘር ያለው ፍቅርና እነርሱን ለማዳን ያቀደው ዕቅድ በነቢያት ትምህርት ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። [...] እና ዛሬም የእርሱን የወይን እርሻ ለመንከባከብ እንደ ታማኝ ገበሬዎች ተቆጥረው ለተቀመጡት ለቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር መልዕክት በጥንቱ ነቢይ ከተነገረው ያ መልዕክት በቀር ሌላ አይደለም፡ “በዚያም ቀን ለተወደደው የወይን ቦታ ተቀኙለት። እኔ እግዚአብሔር ጠባቂው ነኝ፤ ሁልጊዜ አጠጣዋለሁ፤ ማንም እንዳይጐዳው በሌሊትና በቀን እጠብቀዋለሁ። ” (ኢሳይያስ 27:2-3)”

EGW (Prophets and Kings, p. 22)

# አባሪ: የኤለን ጂ. ኋይት ትንቢታዊ ጥሪ

ኤለን ጉውልድ ሀርመን የመጀመሪያ ራዕይዋን የተቀበለችው በታህሳስ 1844 የ17 ዓመት ልጅ እያለች ነበር።

ዊሊያም ሚለር የዳንኤል 8:14 ትንቢትን በ1843 የኢየሱስን ምጽዓት ያውጃል ብሎ ተርጎሞት ነበር። ሲቀጥል ደግሞ ምጽዓቱ በጥቅምት 22, 1844 ነው ብሎ ነበር። ኢየሱስ ግን አልመጣም ነበር።

በዚህ አውድ ውስጥ ኤለን ከምድር ወደ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም የሚመራ መንገድ ላይ የአድቬንቲስት አማኞች ኢየሱስ እየመራቸው ወደ ቅድስቷ ከተማ ሲጓዙ ታያት። አይናቸው በኢየሱስ ላይ ከተተከለ መንገዱን ተከትለው ይሄዱ ነበር። አይናቸውን ከእርሱ ላይ ካነሱ ግን ከመንገዱ ይወድቁ ነበር።

እግዚአብሔር በዚህ ራዕይ አማኞቹን በትክክለኛ መንገድ ላይ መሆናቸውን አረጋገጠላቸው። ኤለንን ወዲያው ያመኗት ጥቂቶች ቢሆኑም በሂደት እንደ ነቢዩት ተቀባይነት ልታገኝ ችላለች። የእርሷ መልዕክቶች የአድቬንቲስት ሕዝብን ከጅምሩ እያበረታቱና እየመሩ እስከዛሬ ድረስ ቀጥለዋል።



